# GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
# DEPARTMENT OF HEALTH

## Human Papillomavirus (HPV) ክትባትን ላለመከተብ መምረጥን ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

**ይህንን ቅጽ አጠናቆ ለመሙላት የሚያስፈልጉ መረጃዎች**

**ክፍል 1**: የተማሪውን ስም ይመዝግቡ

**ክፍል 2**: የወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተማሪ (18 ዓመት ከሞላው ወይም ከዚህ በላይ ከሆነው) የኤች አይቪ (HPV) መረጃ ፍሬ ነገር

| **ክፍል 1፤ የተማሪ መረጃ (Section 1: Student Information)** | | | |
|---|---|---|---|
| የትምህርት ቤት ስም፤ | | | |
| የተማሪው ስም፤ | | የልደት ዘመን: | ክፍል፤ |
| የመንገድ አድራሻ፤ | ከተማ/ስቴት፤ | ዚፕ ኮድ፤ | ስልክ፤ |
| የጤና ሞግዚት ሰጭው መድኅን ድርጅት ስምና አድራሻ፤ | ከተማ/ስቴት፤ | ዚፕ ኮድ፤ | ስልክ፤ |

ከ 2009 ጀምሮ እና እንዲሁም ከ ዲሲ 17-10 ሕግ and in accordance with (D.C.Law17-10) (Human Papillomavirus Vaccination and Reporting Act of 2007) (ከሰው ፓፒሎማ ቫይረስ ክትባትና ከ 2007 ሪፖርት ሕገ ደንብ) ለመጀመሪያ ጊዜ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ 6ተኛ፣ 7ተኛ፣ እና 8ተኛ ክፍሎች የሚገቡ የሴት ተማሪዎች ወላጆች ወይም ሕጋዊ አሳዳጊዎች፣ ሴቶች ተማሪዎች ልጆቻቸውን የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚመለከቷቸው በምሆኑ እነዚህ ጉዳዮች ከግምት እንዲያዝሏቸው የሚያረጋግጡላቸው የምስክር ወረቀት ወይም ማሰረጃዎች እንዲያቀርቡ ይጠበቃል።

1. የ Human Papillomavirus (HPV) ክትባት የወሰዱ፣ ወይም
2. በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ የ HPV ክትባት ያልተከተቡ፤
    - ሀ. በበጎ ቅን መንፈስ፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ በጽሑፍ ለዋናው ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ባለሥልጣን ክትባቱ ከመንፈሳዊ ወይም ሃይማኖ ታዊ እምነቱን ጋር የሚጋጭ መሆኑን በጽሑፍ ተቃውሞውን ገልጿል።
    - ለ. የተማሪው ሀኪም ወይም የእሱ ተወካይ ወይም የሕዝብ ጤና ጥበቃ ባለሥልጣናት፣ ከጤና አንጻር ክትባቱ የማይደገፍ እና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ለትምህርት ቤቱ ማስረጃ በጽሑፍ አቅርበው እንደነበረ እና፣ ወይም
    - ሐ. ወላጅ ወይም ሕጋዊ ሞግዚት፣ ስለ HPV መከላከያ ክትባት ጠቀሜታ አስፈላጊነት ጉዳይ ከተገለጸለት በኋላ፣ ወላጅ ወይም ሕጋዊ ሞግዚት የሆነው ሰው በገዛ ራሱ ፍላጎት እና ምርጫ ልጁ ወይም ልጆቹ ክትባቱን እንዳትወስድ ወይም እንዳይወስዱ በመወሰን ክትባ ቱን የማይፈልገው እና የማይወስድ መሆኑን አምኖ ምርጫ አድርጓል።

| **ክፍል 2፤ የተማሪው መረጃ (Section 2: Student Information)** |
|---|

### Human Papillomavirus (HPV) ክትባት ላለመውሰድ የመወሰን ምርጫ

የ HPV ክትባት ከቅድመ ዐሥራዎቹ የእድሜ ገደብ በፊት ለሚገኙ ሴት ልጆች ከተሰጠ፣ የማኅጸን መተላለፊያ መተላለፊያ ቱቦዎች ነቀርሳ (cervical cancer) እና አባለዘር ብልት ላይ ከሚወጡ ኪንታሮቶች (genital warts) ስለሚሰጠው የመከላከል ጠቀሜታ መረጃዎች ተሰጥቶኝ እና ይህንንም የተ ሰጠኝን መረጃም መርምሬ ተመልክቻለሁ። በ HPV በሽታ ስለመለከፍ እና እንዲሁም በ HPV በመለከፍና እና የማኅጸን መተላለፊያ ቱቦዎች በነቀርሳ መያዝ መካከል ስለሚኖረው የግንኙነት ትስስር አደጋ ከተገለጸልኝ በኋላ፣ ከላይ ስሟ ለተጠቀሰው ተማሪ ልጄ የ HPV ክትባት እንዳይሰጥ መርጫለሁ። ይህን ጉዳይ ወደፊት በማናቸውም ጊዜ እንደገና መርምር ማጣራት እና ማየት እንደምችል፣ እንዲሁም የሚያስፈልገውን ክትባት ላሟላ እንደምችል እገነዘ ባለሁ።

______________________________ ________________
የወላጅ/አሳዳጊ ወይም የተማሪው ፊርማ (18 ዓመት ወይም ከዚህ በላይ የሆነው) ቀን

______________________________
በጉልህ የተጻፈ የወላጅ/አሳዳጊ ወይም የተማሪው ስም (18 ዓመት ወይም ከዚህ በላይ የሆነው)

**GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA**
**DEPARTMENT OF HEALTH**

## በሰው አካል ላይ ስለሚወጣ ኪንታሮት መሰል ተዋህሳውያን እባጭ (HUMAN PAPILLOMAVIRUS (HPV)) መረጃ ፍሬ ሀሳብ

የሰው አባለ ዘር አካል ላይ የሚወጣ Genital human papillomavirus (HPV) (ኪንታሮት መሰል እባጭ) በዩናይትድ ስቴትስ እጅግ በጣም የተለመደ ተላላፊ የአባለ ዘር በሽታ ነው። ወደ 100 የሚጠጉ የ HPV ዐይነቶች ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ተላላፊ በሽታዎች ምልክት የማያሳዩ ከመሆና ቸውም በላይ በራሳቸው የሚጠፉ ናቸው። HPV በመጀመሪያ ደረጃ በሴቶች ላይ የማኅጽን መገናኛ ቱቦዎች ነቀርሳ (cervical cancer) የሚያደ ርስና እንዲሁም በጣም በብዛት ባልተለመደ ዝቅ ባለ ሁኔታ በወንዶች እና በሴቶችም ላይ ነቀርሳ ሊፈጥር የሚችል በመሆኑ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በተጨማሪም፣ በብልት አካባቢ እና እንዲሁም በላይኛው የመተንፈሻ አካላችን ላይ ኪንታሮቶች (warts) ያስከትላል። ለ HPV በሽታ መድኃ ኒት የሌለው ሲሆን፣ የሚያስከትለው ችግር ሕክምና ሊደረግለት ይችላል።

በዩኤስ ወደ 20 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በበሽታው የተጠቁ ሲሆን፣ በየዓመቱ ደግሞ 6.2 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች በዚሁ በሽታ ይያዛሉ። HPV በግብረ ሥጋ ንክኪነት አማካይነት ይዛመታል። ከመቶ 50 እጅ (50%) በላይ የሚሆኑ፣ የግብረ ሥጋ ተግባር ማካሄድ የሚችሉ ወንዶችና ሴቶች በሕይወታቸው ዘመን ውስጥ በበሽታው አንድ ጊዜ ይያዛሉ። በዩኤስ በየዓመቱ፣ 10,000 የሚሆኑ ሴቶች በማኅጸን መገናኛ ቱቦዎች ነቀርሳ (cervical cancer) የሚያዙ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 3,700 የሚሆኑ ሴቶች በዚሁ በሽታ ጠንቅ ይሞታሉ። ይህ፣ በዲሲ፣ በማኅጸን መገናኛ ቱቦዎች ነቀ ርሳ የሚኞች ቁጥር ከብሄራዊው የሚኞች አማካይ ቁጥር በላይ ከፍ ብሎ ይገኛል።

ለ HPV መከላከያ የሚሰጥ ክትባት፣ ሙሉ ሕያውነት የሌላቸው (በጣም የተዳከሙ ተዋሕሳውያን) በመሆኑ ከ 4 ዋና ዐይነት ተውሳኮች የሚከላከ ለው ለዚህ ነው። እነዚህም 70 እጅ (70%) ይህል የማኅጸን መገናኛ ቱቦዎች ነቀርሳ የሚያስከትሉት 2 ዐይነት ተዋሕሳውያንን ይይዛል። የ HPV ክትባት አብዛኛዎቹን የአባለ ዘር ኪንታሮቶችን እና እንዲሁም የማኅጽን መገናኛ ቱቦዎች ነቀርሳ (cervical cancer) ሊከላከል ይችላል።

በግብረ ሥጋ ንክኪነት ጊዜ መከላከያ ማድረግ፣ ለረጅም ጊዜ ዘላቂ ሊሆን እንደሚገባው የሚጠበቅ ሲሆን፣ ክትባት ብቻውን ከሁሉም የማኅጸን መገ ናኛ ቱቦዎች ነቀርሳ ሊያደርሱ ከሚችሉ የ HPV ዐይነቶች ጠንቅ መከላከል ስለማይችል፣ አሁንም ቢሆን ክትባት የወሰዱ ሴቶች የማኅጸን መገናኛ ቱቦ ዎች ነቀርሳ የማጣሪያ ምርመራ ማድረግ ይገባቸዋል።

የ HPV ክትባት፣ እድሜአቸው ከ 11-12 ዓመት ለሆናቸው ሴት ልጆች በየጊዜው ያስፈልጋቸዋል። የሕክምና ዶክተሮች 9 ዓመት እድሜ ላላቸ ውም ሴት ልጆች ጭምር ክትባቱን ሊሰጡ ይችላሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት የሚያደርጉ ልጃገርዶች ከዚህ ቀድም በ HPV በሽታ ያልተያዙ ስለነበሩ አሁን ግን ከዚህ የመጀመሪያቸው ከሆነው ንክኪነት በፊት ሴት ልጆች የ HPV ክትባት መውሰድ እጅግ አስፈላጊ ነው። ለእነዚህ ልጃገረዶች፣ ክትባቱ ከሚያተኩርባቸው 4 የ HPV ዐይነቶች 100 እጅ (100%) እነዚህ ከሚያስከትሉት በሽታዎች ይከላከልላቸዋል። ሆኖም አንዲት ልጃገርድ ወይም ሴት የ HPV ዐይነቶች ከሆኑት በአንዱ ተይዛ የምትገኝ ከሆነ፣ ክትባቱ ከእንዲህ ያለው ዐይነት በሽታውን ማስወገድ አይችልም። በ HPV በሽታ የተያዙ ልጃገረዶች ወይም ሴቶች ክትባት እንዲወስዱ ይመከራሉ።

በተጨማሪ፣ እድሜአቸው 13-26 ለሆኑ እና ከዚህ በፊት ቀደም ብሎ ክትባቱን ላልወሰዱ ልጃገረዶች፣ ክትባቱ የሚታዘዝ ነው። ይህም ክትባት ከሌ ሎች ከሚፈለጉ ክትባቶች ጋር አብሮ ሊሰጥ ይችላል።

**የ HPV ክትባት መወሰድ እንዳለበት እንደ 3 - ልከመጠን ተከታታይ ክትባቶች ይሰጣል። (HPV vaccine is given as a 3-dose series)**

- **1ደኛ ልከመጠን፤ አሁን**
- **2ተኛ ልከመጠን፤ 1ደኛው ልከመጠን ከተሰጠ 2 ወራት በኋላ**
- **3ተኛ ልከመጠን፤ 1ደኛው ልከመጠን ከተሰጠ 6 ወራት በኋላ**

የእርሾ ሻጋታ (yeast) አካላቸውን የሚያስቆጣ፣ የሚጎዳ እና ለሕይወት ጠንቅ የሆነ ሁኔታ የገጠማቸው፣ ቅሪት የሆኑ፣ እና/ወይም ከመጠንኛ እስከ ጠንካራ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ክትባቱን መውሰድ የለባቸውም። ክትባቱ የሚያስከትለው ጣጣ አብዛኛውን ጊዜ ቀለል ያለ ሆኖ፣ ሰውነት ማሳከክን ጨምሮ፣ የሕመም ስሜት፣ መርፌውን በተወጉበት አካባቢ ላይ የሰውነት መቅላት እና ከቀላል እስከ ከባድ ደረጃ የሚያደርስ ትኩሳት ናቸው።,

---

***ተጨማሪ መረጃዎች የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ እባክዎን የጤና ጠባቂ ሞግዚትዎን ያነጋግሩ። ከዚህም በተጨማሪ ዲሲ የጤና መምሪያ የክትባት ፕሮግ ራምን (D.C. Department of Health Immunization Program) በ (202) 576-9342 ወይም የበሽታዎች መቆጣጠሪያ እና መከላ ከያ ማዕከላትን (the Centers for Disease Control and Prevention (CDC)) በ 1-800-CDC-INFO (1-800-232-4636) ደው ለው ያነጋግሩ።***

Updated January 2011